የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 18
ADDIS ABABA 29th March, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፮/፪ሺ፲፬

ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ………………………ገጽ ፲፬ሺ፩፻

## Content

Regulation No. 496/2022

Wonji/Shoa Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation…...Page 14100

## ደንብ ቁጥር ፬፻፺፮/፪ሺ፲፬

## ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፮/፪ሺ፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ከዚህ በኋላ “ፋብሪካ” እየተባለ የሚጠራው የፌደራል የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

## REGULATION NO. 496/2022

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF WONJI/SHOA SUGAR FACTORY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as "Wonji/Shoa Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 496/2022”.

**2. Establishment**

1/ Wonji/Shoa Sugar Factory, hereinafter referred to as “The Factory”, is hereby established as a Federal Public Enterprise.

2/ Wonji/Shoa Sugar Factory shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

## ፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶ መሠረት የፋብሪካውን የንግድ ሥራ ጉዳዮች የመምራት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የፋብሪካው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

## ፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ዋና መሥሪያ ቤት ወንጂ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌላ ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## ፭. <u>ዓላማ</u>

ፋብሪካው የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩/ የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ተክሎችን ማልማት፤

፪/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶች እና ተጓዳኝ ምርቶችን ማምረት፤

፫/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችንና ተጓዳኝ ምርቶችን በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኩል ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

፬/ የፋብሪካውን የስኳር ልማት ማስፋፊያ መልሶ የማደስ ፕሮጀክቶችን ማቀድና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፭/ በአዋጪነትና በውጤታማነት ላይ ተመስርቶ እንደአስፈላጊነቱ ከአገዳ አብቃዮች ጋር ውል ገብቶ መስራት፤

## 3. <u>Supervisory Authority</u>

Without prejudice to the right of the Ethiopian Sugar Industry Group Pursuant to Article 550 of the Ethiopian Commercial Code to direct the business affairs of the factory, the Public Enterprises Holding and Administration shall be the supervisory authority of the Factory.

## 4. <u>Head Office</u>

The head office of Wonji/Shoa Sugar Factory shall be in Wonji town and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

## 5. <u>Purpose</u>

The purposes for which the Factory is established are:

1/ To grow sugarcane and other sugar yielding plants;

2/ To process and produce sugar, sugar by-products and co-products;

3/ To supply sugar and sugar by-products and co-products to local as well as foreign market through the Ethiopian Sugar Industry Group;

4/ To plan sugar development expansion and overhaul projects within the Factory and implement same upon approval;

5/ To work in agreement with sugarcane growers based on feasibility and effectiveness;

፮/ ለፋብሪካው የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት መስራት፤

፯/ ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የሸንኮራ አገዳ እርሻ መሬት በሊዝ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ ማግኘትና በይዞታው ሥር ማድረግና ማልማት፤

፰/ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫና የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል ተደራድሮ በመፈረም ገንዘብ መደበር፤

፱/ የፋብሪካውን የማምረት አቅም የሚጨምሩ አዲስ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትን ሥልጠናንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር መደራደርና ውል መፈረም፤

፲/ በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ከሚከናወኑት በጋራ ማዕቀፍ ከሚገዙት ግዢዎች ውጪ ያሉትን የግዢ ውሎች በመዋዋል ግዢ መፈጸም፤

፲፩/ ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ሥራዎችን መሥራት፡፡

## ፮. ካፒታል

ለወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፲፭ ቢሊዮን ፰፻፹፮ ሚሊዮን ፱፻፶፭ ሺህ ፫፻፯ ብር ከ፳፰ ሳንቲም (አስራ አምስት ቢሊዮን ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ሶስት መቶ ሰባት ብር ከሃያ ስምንት ሳንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፫ ቢሊዮን ፱፻፸፩ ሚሊዮን ፯፻፴፰ ሺህ ፰፻፳፮ ብር ከ፹፪ ሳንቲም (ሶስት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ

6/ Work to produce the required trained manpower in number, type and quality;

7/ Acquire use right on lease or by other legal means and develop agricultural land for sugarcane plantation;

8/ In accordance with the policy direction and Directives issued by the Ministry of Finance, negotiate and sign loans with domestic as well as foreign financial institutions;

9/ Enter into a contract with other companies for introducing new technologies or training and other matters of importance that improve the Factory's productivity;

10/ Execute procurements those are not included in the common procurement package that is carried out by The Ethiopian Sugar Industry Group;

11/ Engage in any other activity that is necessary to accomplish its purposes.

## 6. Capital

The authorized capital of Wonji/Shoa Sugar Factory is Birr 15,886,955,307.28 (Fifteen Billion Eight Hundred Eighty Six Million Nine Hundred Fifty Five Thousand Three Hundred Seven Birr and Twenty Eight Cents) of which Birr 3,971,738,826.82 (Three Billion Nine Hundred Seventy One Million Seven Hundred Thirty Eight Thousand Eight Hundred Twenty Six Birr

ሰላሳ ስምንት ሺ.ህ ስምንት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከሰማንያ ሁለት ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. **ኃላፊነት**

ፋብሪካው ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. **የቆይታ ጊዜ**

ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

፱. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

and Eighty Two Cents ) is paid up in cash and in kind.

7. **Liability**

The Factory shall not be held liable beyond its total assets.

8. **Duration**

Wonji/Shoa Sugar Factory is established for an indefinite duration.

9. **Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 29th Day of March, 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**